# ኢትዮጵያ፣ከፋፋይ ህጎቿና የዶክተር አብይ ፈተናዎች

በአዲስ ተስፋ

ለህዝባችን መሚገታችን አልያም እውነት እንዲዎጣ መፈለጋችን በብዙ ወገኖቻችን ዘንድ ዘረኛ እያሰኘን ይገኛል። እንደ እውነቱ ከሆነ ዘረኛ የሚለው ትርጉም በእርግጥም ከገባን አገራችን አሳሳቢ በሆነ የዘር ሰንሰለት ታስራለች። ዘረኛ ማለት ከራሱ ዉጪ የማይታየው ፣ሌላውን የሚጠላ፣ በሌላው የሚቀና ፣ ስስታም ወይም ጠባብ የሚሉ ተለዋጭ ትርጉሞች አሉት። ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ፍትህ፣ እኩልነትና እውነት የገነኑ ከሆነ ነው። ዘረኞች ደግሞ እኩልነትን ፣ ፍትህንና እውነትን አይፈልጉም። አገር ያጨበጨበላቸው ዶክተር አብይ ለውጥ አመጡ ሊባል የሚችለው ደግሞ እውነተኛ ዲሞክራሲ ፣ ፍትህና እኩልነት እንዲረጋገጥ መሰረታዊ እርምጃዎችን ከወሰዱ ብቻ ነው። ያ ደግሞ እስካሁን አልተጀመረም። በሃገራችን ላለፉት ሶስት አስርት አመታት የተዘራው ዘር አሁን ፍሬውን እያጨድን እንኳ የዘርና የቋንቋ ፖለቲካ አግባብ እንደሆነ ይሰበክልናል። ብዙዎቻችን የርዋንዳ እጣ ፋንታ እንዳይደርሰን እንላለን። በሩዋንዳ በተወሰኑ ቀናት ብቻ ከስምንት መቶ የሚልቁ ዜጎች አልቀው ስለነበረ የዚያንን መጥፎ ገጽታ ብቻ እያስታውስን እንደ ሩዋንዳ እንዳንሆን እንላለን። በመሰረቱ በሩዋንዳ የነበረው መጥፎ ገጽታ እኮ በሃገራችን ሆኗል። ሟርተኛ እንደማልባል ተስፋ አደርጋለሁ። እስኪ መለስ ብለን ይህ የዘርና የቋንቋ ፖለቲካ አገራችን ከተጀመረ ጀምሮ ያለቁትን ንጹሃን እንቁጠር። ሁሌ አማራ አማራ እያላችሁ ለምን ትጮሃላችሁ? ለምትሉን በርግጥም ሊያሰለቻ ችሁ ይችላል።ለመሆኑ በሃረርጌ፣ በባሌ፣ በአርሲ፣ በወለጋ፣በኢሉባቦር፣ በሸዋ ፣ በከፋ ፣ በደቡብ ጉራ ፈርዳ፣ በአሶሳ፣ በጅግጅጋ፣ በድሬዳዋና በተቀሩትም የሃገሪቱ ክፍሎች ስንት አማራ ነው ያለቀው፣ በትግራይስ የሁለቱን ጊዜ የህዝብ ቆጠራ ውጤቶች ስንመለከት የጎደለው በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠረው አማራ የት ሄዶ ነው ?እንደምናውቀው በኦፊሴላዊ መንገድ ከትግራይ አማራ አልተባረረም ፤ ነገር ግን በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር አማራ ጎድሏል። አሁንም መደጋገሙካላሰለቼ በቀር በህጋዊ መንገድ በፓርላማ ከሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ሺህ በላይ የሆነ አማራ ጠፍቷል ተብሎ ሪፖርት ተደርጓል። ዛሬ ድረስ ማቆሚያ ያጣው የአማራ ስደትና ግድያ ከሩዋንዳ በብዙ እጥፍ ዜጎቻችን አልቀዋል። ይህ ሁሉ ሆኖ እያለ ዶክተር አብይ በግለጽ አማራ ከሌላው የተለየ በደል አልደረሰበትም ሲሉ በቁስላችን ላይ እንጨት ስድ ደዋል።

በበኩሌ በዚህ ንግ ግራቸው በጣም አዝኛለሁ። ምክን ያቱም በሽታው መጀመሪያ ካልታዎቀ መድሃኒት መስራት ወይም ማግኘት አይቻልምና። በርግጥ አሁን አሁን እየሞተ ያለው አማራ ብቻ አይደለም። ቢሆንም ግን በመዋቅራዊ መንገድ ላለፉት 30 አማታትና ዛሬም ቢሆን እያለቀና እየተሳደደ ያለው አማራው ነው። ዶክተር አብይን ከማማታችን በፊት በግልጽ ልንነግራቸው ይገባል። ጨኸቱ ፣ ሩጫው፣ እሽቅድምድሙ ያንን መዋቅራዊ መንገድ ማስቀጠሉ ላይ ሆኗል። ከዚህ በፊት በሞነጫጨካቸው ጽሁፎች ዶክተር አብይን የሞገትኳቸውም ስልጣኑን እንደያዙ ባላቸው ህገመንግስታዊ ስልጣን አንዳንድ ህጎችን መሻርና በምክርቤታቸውም እንዲሻር ማድረግ እንዲችሉ ነበር። አንዳንድ ወገኖች ይህ ጊዜው አይደለም ፤ ጥያቄህ ፈጠነ ብለውኝ ነበር።ከቤንሻንጉል ክልል ህገመንግስት በመነሳት አይን ያውጡና የተወሰኑ የአገራችንን ነገዶች ባለቤት ላለማድረግ የተሰራውን ደባ ለማሳየት ሞክሬ ወደፊት ወደ ሌሎችም የከተሞችና የክልሎች ህጎች እንደምመለስ ቃል በመግባት ነበር ጽሁፌን ያቆምኩ። ይሁንና ጭራሹኑ የሀገራችን ህዝብ በሙሉ የሚኖርባትን አዲስ አበባን በተመለከተ ውዝግብ ሲነሳ ሳስተውል የችግራችን ጥልቀት ምን ያህል የገዘፈ መሆኑ ታይቶኛል። በርግጥ ፖለቲከኞች ሁሌም የህዝብ ድጋፍ የሚያገኙበትን ስሜትን የሚያነሳሳ ነገር ከመፈለግ ወደ ኋላ አይሉም። ቀድሞ ነገር ሁሉንም ባለማስተዋል እያጨበጨብን ስንቀበል የተበላሸ ነገር እንደሚኖር መገመት ነበረብን። ጃዋር መሃመድ ወደ አገር ቤት ሲገባ በፌስ ቡክ ግጼ ጅዋር በእውነት መስመሩንና ጥላቻውን ቀይሮ ከሆነ የተናገራቸውን አስቀያሚ ቃላት በመዘርዘር የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ ይገባዋል በማለት ''ነገረ ጃዋር ''የምትል ጽሁፍ ለጠፍኩ። የማደንቃቸውና የማከብራቸው ታላላቅ ሰዎች ሳይቀሩ ምን ማለትህ ነው? ጃዋር እኮ የዘመናችን የፖለቲካ ሳይንቲስት ነው ፤ አማራንና ኦሮሞን በሳምንታት አንድ ያደረገ ጀግና ፤ የድሮን ታሪክ በማምጣት አሁን ጥላቻ መስበክ የለብህም አሉኝ፤ ለማከብራቸው ለእነዚያ ሰዎች ስልም ያችን ጉደኛ መልእክት ከፈስቡክ ገጼ አዎረድኳት።

ነገር ግን ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ሳይንቲስቱ ጅዋር ኦሮምያን መገንጠል እችላለሁ፣ አሁን በሃገራችን ሁለት መንግስት ነው ያለው አንዱ በእኔ ይመራል ወዘተ በማለቱ የተቆጡኝ ሰዎች አንተ ትክክል ነበርክ አሉኝ። ከሰሞኑ ደግሞ የኦነጉ መሪ አቶ ዳዎድ ኢብሳ ''ኦነግ ትጥቅ አልፈታም ፤ እንደዚህ ያለ ውልም ከመንግስት ጋር የለንም '' ፤ በማለት በቴለቪዥን ተናገሩ። የአዲስ አበባ ብጥብጥ፣ የጃዋር መሃመድ የፈለገውን መናገር(ከህግ ውጪ) የቤንሻንጉሉ ፍጅት ፤ የኦነግ ትጥቅ አልፈታም ማለትና ሌሎችም አሰገራሚ ነገሮች መነሻቸውም መድረሻቸውም ህገ መንግስቱና ዶክተር አብይ በመለዳደስ ሊጠግኑት የሚሞክሩት የዘር ፖለቲካ ነው። እስኪ ከከተሞች ህጎች የአዳማን ህግ እንመከት።በነገራችን ላይ የአዲስ አበባ ግርግር

እንደተባለው በአዲስ አበባ ላይ የባለቤት ጥያቄ ለማንሳት ብቻ ያለመ ነው ማለት ሞኝነት ነው፤ ይልቁንም በሌሎች ከተሞች ያለው ጥያቄ ለጊዜው ተረስቶ ሁሉም ትኩረቱ በ አዲስ አበባ እንዲሆን የታሰበም ይመስላል። የዶክተር አብይ ህግን አስከብራለሁ እኩልነትና ፍትህ በሃገራችን እንዲሰፍን እሰራለሁ እውነተኛ ዲሞክራሲ በሃገሪቱ ይሰፍናል ለፈፋ ከንግግር ውጪ ሌላ ሊያመጣው የሚችል ፋይዳ የለውም። ምክንያቱም እነዚህ ከፋፋይና አድሎአዊ ህጎች በስራ ላይ ናቸውና። ባለፈው ከቤንሻንጉል ክልል የተነሳሁትም የደብረዘይት፣ የናዝሬት፣ የድሬዳዋ፣ የሃረርንና የሌሎችንም ከተሞች ህግ ስለማላውቀው ሳይሆን በተለይ የዐማራንና የኦሮሞን ህዝብ ለመነጣጠልና ለማጋጨት አስቀደሞ የተሰራው በርካታ ተንኮል ተዘርዝሮ ስለማያልቅ አንባቢዎቼም ባያዝድ የሆንኩ እንዳይመስላቸው ነበር። አሁን ግን እንደጀመርኩ እቀጥላለሁ። በነገራችን ላይ የአዳማን ህግና እውነታውን ስንጨዋወት ጋዜጠኛና አክቲቪስት ተስፋየ ደጉ እርሱም የሰራውን መረጃ ላከልኝና አየሁት። የሚገርመው እኔ ባለፈው የቤንሻንጉሉን በሰራሁበት መንገድ ነበር የጻፈው እኔም ጽፌው ስለነበር ጨምቄ እነሆ ብያለሁ። አስቀድሜ መግለጽ የምፈልገው የዚህ መረጃ አላማ በኢትዮጵያ አሁን ባለው የአከላለል ሁኔታ የየክልሎችን ቋንቋ መናገር የማይችሉ ዜጎች ምን ያህል ባይታዎርና የተገለሉ መሆናቸውን ለማሳየትና ዜጎች በሃገራቸው በተለይም በዚህ በምንኖርበት የ21ኛው መቶ ክፍለዘመን እንደ ስደተኛ የሚቆጠሩበት ብቸኛ ሃገር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን ለማሳየትም ጭምር ነው።ሁላችንም እንደምናውቀው የአዳማ የቀደሞ ወይም የአማርኛ ስሟ ናዝሬት ነው። ከአሰያየሙ ጀምሮ የተዎሰደው ፖለቲካዊ እርምጃ ህዝብን ከፋፋይ ነበር። የኦሮምኛ መጠሪያዋ አዳማ ነው ቢባል ምንም ስህተት የለውም። ነገር ግን ታሪካዊውንና ህዝብ የተለማመደውን ያንን ስም ከዛሬ ጀምሮ ባለቤት ስለሆንኩ ከተማይቱ እንዲህ ተብላ እንድትጠራ ወስኛለሁ ብሎ ህዝብ ተቀበለውም አልተቀበለውም በሃይል መጫን ከበስተጀርባው ያለውን ፖለቲካዊ ሻጥር እንጂ ሌላ ነገር አያሳይም።ስሞች ብቻ እንደሆኑ መግለጹ በየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ቅሬታ ኣያመጣም። በሃገራችን ባለፉት ፴ አመታት የተደረጉት የአካባቢ ስም ለውጦች ግን ህዝብን ለመከፋፈል ሆን ተብሎ ተደርጓል። በርግጥ ሰረኛ ፖለቲከኞች እንዳሰቡት የፈለጉትን ውጤት አላመጣላቸውም። ስም በተለያየ ቃንቋ የተለያየ ሊሆን ይችላል። እንኳንስ የአካባቢ ስም የሰው ስም እንኳ በተለያዩ ስሞች የተልያየ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ጆንሰን የሚለው የእንግሊዘኛ እውቅ ስም በደች ያንሰን በመባል ይጠራል። ቪሊየም የሚለው የእንግሊዘኛ ስምም በጀርመንኛ የሹለም በመባል ይታውቃል። በአጠቃላይ ስም ከስምነቱ ውጪ የሚያመጣው ፋይዳ አለ ተብሎ ባይገመትም ፖለቲካዊ ውሳኔ መሆን ግን አልነበረበትም።

ወይም በቀላሉ የአማርኛና የኦሮምኛ ስሞች ብቻ እንደሆኑ መግለጹ በየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ቅሬታ ኣያመጣም። በሃገራችን ባለፉት 30 አመታት የተደረጉት የአካባቢ ስም ለውጦች ግን ህዝብን ለመከፋፈል ሆን ተብሎ ተደርጓል። በርግጥ ሴረኛ ፖለቲከኞች እንዳሰቡት የፈለጉትን ውጤት አላመጣላቸውም።በነገራችን ላይ ይህ የስም ለውጥ የተደረገው በኦሮምያ ብቻ ሳይሆን በቀሩትም ክልሎች ነበር። መሰረታዊ እሳቤው የዐማራን ማህበረሰብ ማሸማቀቅና ስነልቦናዊ ጫና ማድረግ ነበር። ለሚሳሌ የሚከተሉት የከተሞች ስሞች ተቀይረዋል። አስበ ተፈሪ፣ አለምያ፣ ጅጅጋ፣ አዋሳ፣ ደብረ ዘይት፣ ናዝሬት፣ አዲስ አበባና ሌሎችም። በየቋንቋዎች የተለየ ስያሜ መሰጠቱን አልቃዎምም። ነገር ግን ነፍጠኞች አልያም ሰፋሪዎች የሰጡት ስም በመሆኑ ይቀየር የሚለው ግን ከፋፋይ ብቻ ሳይሆን ለሀገራችን ለዎደፊት ሰላም አስተዋጽ ኦ የለውም። ወደዋናው ሃሳቤ ስመለስ ናዝሬት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1999 ዓም በተደረገው የቤቶችና ህዝብ ቆጠራ ውጤት መሰረት የከተማዋ ነዋሪ ብዛት 220,212 ነበር። በመሆኑም በመቶኛ በነገድ ስብጥሯ ስናሰላው 39.02% ኦሮሞ፤ 34.53% ዐማራ፤ 11.98% ጉራጌ፤ 5.02% ስልጤና ሌሎች 9.45% ነበር።። ይህንን መረጃ በተተከለው የቋንቋ ፌደራል ሥርዓት መሰረት ብንተነትነው አዳማ/ናዝሬት በኦሮምያ ስር የተካለለ በመሆኑ 39.02%የሚወክለው የኦሮሞ ማህበረሰብ አስተዳደራዊ ፣ ትምህርትንና የፍትህ ስርዓቱን ይመራል ። ይህ ማለት ወደ 60 % የሚሆነው የተቀረው ማህበረሰብ ወደ 40 % በሚሆነው ይደፈጠጣል ማለት ነው ። የቋንቋን ስርጭት በአዳማ/ናዝሬት እንመልከት እስቲ ። ከነዋሪው ውስጥ 59.25% አፍ መፍቻው አማርኛ ሲሆን ፣ 26.25% ደግሞ ኦሮምኛ ፣ 6.28% ጉራጊኛ ሲሆን የተቀረው 8.22% የተለያዩ አፍ መፍቻ ቋንቋን የሚወክል ነው ። ይህ ስታትስቲክስ የሚያሳየው ቁም ነገር ወደ 60 % የሚሆነው የአዳማ/ናዝሬት ነዋሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋው አማርኛ ቢሆንም በክልሉ የስራ ቋንቋ በኦሮምኛ ፍርድ ቤትና ትምህርት ቤት በግድ እንዲጠቀም ይገደዳል ማለት ነው ። ይህም ማንም ልጅ በአፍ መፍቻ ቋንቋው የመማር መሰረታዊ መብት እንዳለው የሚደነግገውን መሰረታዊ የህጻናት መብትን ይጋፋል ። ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማር ሲገባቸው ሳይወዱ በግድ በክልል ቋንቋ እንዲማሩ መደረጋቸው የሚኖረውን ሥነ ልቦናዊ ጫናም ሆነ ዕውቀትን ለመቅሰም የሚገጥማቸውን ተግዳሮት ለመገመት የልጅነት የትምህርት ዘመናችንን ማስታወስ በቂ ነው ።

ሌላው አሳዛኝ ነገር 60% የሚወክሉት አዳማ/ናዝሬት ላይ ተወልደው ያደጉ ኦሮሞ ያልሆኑ ዜጎችና 73 % የሚሆኑ አፍ መፍቻቸው ኦሮምኛ ያልሆኑት የከተማዋ ነዋሪዎች በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ወይም በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ተቀጥረው

እንጀራ ለመብላት ያላቸው እድል የመነመነ መሆኑ ነው ። ታዲያ ይህንን የመረረ እውነት ተሸክሞ ፍት ህ፣ እኩልነትንና ዲሞክራሲን ማስፈን የሚቻለው እንዴት ነው?ለዚህ ነው ህገ መንግስቱ ራሱ እና ከዚያ የሚመነጩ ህጎች ሁሉ ከፋፋይ አድሎአዊና በህዝብ መካከል ያለመተማመንን የሚያነግሱ ስለሆኑ ዶክተር አብይ ኢትዮጵያዊነትን ለማንገስ ከፈለጉ በቆራጥነት እርምጃ መውሰድ አለባቸው የምንለው። ሰዎች አሁን ኦሮሚያ በሚባለው ክልል ያሉ ኢፍት ሐዊና ከፋፋይ ህጎች ስናነሳ ኦሮሞ ባለመሆናችን አልያም ለኦሮሞ ጥላቻ ያለን እንደሆነ በማስመሰል ፕሮፓጋንዳ ይሰሩብናል። ነገር ግን በርካታ ኦሮሞ ዎገኖቻችን ኢትዮጵያዊነትንና በሁለቱ ህዝቦች መካከል የተቀበረውን የጥላቻ ፖለቲካ በሚገባ ያውቁታል። እኔም እንደ አንድ ዜጋ እኩልነት ፣ፍት ህና፣ ዲሞክራሲያዊ ተጠቃሚነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ከመናፈቅ ውጪ ሌላ ጥማት የለኝም። የታማኝ በየነ አድናቂም ተከታይም ባልሆንም ባለው እውቀትና ችሎታ የሚሰብከውን ኢትዮጵያዊነት ግን አወደዋለሁ።እስኪ የሚከተለውን በጣም ለስላሳ ምሳሌ እንመልከት።አርቲስት ጥላሁን ጉግሳ ከጥቂት ወራት በፊት በአሜሪካን ሃገር ለአርቲስት ሙሉቀን መለሰ የእርዳታ ማሰባበሲያ ፕሮግራም ላይ ስላገኘው አርቲስትና አክትቪስት ታማኝ በየነ በቁጭትና በሚያሳዝን ቅላጼ እንዲህ አለ።'' አንተ እኮ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ብቻ ነህ። አንተ በእውነት ኢትዮጵያዊ ነህ '' በማለት ኢትዮጵያን ለሚጠሉ በእልህ በሚመስል ሁኔታ ገለጸው። በጊዜው የአርቲስት ጥላሁን ናፍቆትና መሻት ምን እንደሆነ መገመት በጣም ቀላል ነው። ምናልባትም በጸና ኢትዮጵያዊ አቋሙ ያጣቸው ነገሮች የከፈላቸው መስዋእትነቶች እንዳሉ መገንዘብ ቀላል ነው። ከጥቂት ወራት በፊት በአሜሪካን አገር ሜኖሶታ ግዛት ዶክተር አብይና አቶ ለማ ከኢትዮጵያውያን ጋር ባደረጉት ውይይት አቶ ለማ በአማርኛ ለመናገር ሲጀምሩ ጥቂት ሰዎች በኦሮምኛ እንዲናገሩ ድምጽቻቸውን ከፍ አድርገው ሊረብሿቸው ሞከሩ። በኢትዮጵያዊነት ስሜት የነደደውንና ሊደግፋቸው የዎጣው ህዝብ ንግግራቸውን መስማት በአማርኛ መቀጠል ነበረባቸው። እናም ቆይቼ በኦሮሚኛ እተረጉመዋለሁ በማለት እንዲቀጥሉ እድል እንዲሰጣቸው ተማጽኑ። በዎቅቱ የነበራቸውን ጭንቀት ግን ፈጽሞ አልረሳውም። ከልባቸው የኢትዮጵያውያንን ስሜት የተረዱት ይመስላል። በአንድ በኩል መላውን ለውጥ ፈላጊ የሚያረካ መልእክት ለማስተላለፍ በሌላ በኩል ደግሞ የዎጡበትን የኦሮሞ ህብረተሰብ በሚፈልገው አኳሁዋን ለመድረስ የነበራቸው ጉጉት ጭንቅታቸውን ፍንትው አድርጎ ያሳይ ነበር። የሆነው ሆኖ እኝህ ሰው'' ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው'' የሚል ሁሉንም ያስፈነጠዘ አባባል ከገዥው ጎራ ያመነጩ ታሪክ ሊረሳቸው የማይችል ሰው ናቸው። ዶክተር አብይ ከሰማይ እንጂ ከምድር በማይመስል መልኩ የኢትዮጵያዉያንን ልብ ያሸነፉት ''ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ ነን'' በሚለው አባባላቸው ነበር። ከላይ ሶስቱም ሰዎች ስለ ኢትዮጵያዊነት በቁጭትና ከልብ በመናገራቸው ለምን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ተደሰተ? ጊዜና ፖለቲከኞች ያመጡብን ጣጣ በመሆኑ እናገረዋለሁ። ሁሉም ከኦሮሞ አብራክ የዎጡ ናቸው። እነዚህ አባባሎች ከአማራው አካባቢ ተነግረው ቢሆን ኖሮ ትምክህተኞች ወይም የቀድሞ ስርዓት ናፋቂዎች ያሉት በማለት ምናልባትም በአሉታዊ መንገድ ስለ አባባሉ እንሰማ ነበር። ነገር ግን ሁለት እጅግ አደገኛ ፕሮፓጋንዳዎች ላለፉት በርካታ አመታት ተነዝተው ስለበር ይህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደ ትንግርት እንዲያየው አድርጎታል።ከእነዚህ ሁለት አደገኛ ፕሮፓጋንዳዎች አንዱ የኦሮሞ ህዝብን በተመለከተ ሲነገረን የኖረው አሉታዊ ገጽታ ነው። ኦሮሞ ጠባብ ነው፣ ኦሮሞ ስለ መገንጠል እንጂ ስለ ኢትዮጵያዊነቱ ደንታ የለውም፣ ኦሮሞ መሪ መሆን አይችልም እና የመሳሰሉት ሆን ተብለው በቀረው ኢትዮጵያዊ ዘንድ እንዲሰርጽ የተደረገው ስራና ከዚህም ጀርባ ያለው ድርጅት ኦነግ ስለመሆኑ መነገሩ ነው። በርግጥ ኦነግም በኦሮሞ ስም እጅግ በርካታ ዎንጀሎችን ሰርቷል። ለምሳሌ በሰማኒያዎቹ መጀመሪያ በአማራ ላይ ለተደረገው ጭፍጨፋና መፈናቀል ቀጥተኛ ተጠያቂ ነው።

አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንዲሉ ሃገራዊ አንድነትን በመሻት እውነታውን መካድ ዋጋ ከማስከፈል ውጪ የሚሰጠው ጥቅም የለም። ኦነግ የኦሮሞ ህዝብን እወክላለሁ ብሎ የትግል አቅጣጫ ቢነድፍም የኦሮሞ ህዝብ ወኪል አለመሆኑ ግን በሚገባ ሊነገረው ብቻ ሳይሆን አንድ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን ብቻ ማዎቅ ይኖርበታል።የትናቱ በደል ይረሳ ቢባል እንኳ ዛሬም ቦምብ እየተዎረወረ ያለው ፣ በአዲስ አበባና በ ዙሪያዋ በተቀሰቀሰው እልቂትና መፈናቀል፣ በበንሻንጉል ጉምዝ ክልል በተደረገው ግድያና መፈናቅል፣ በወለጋ የተለያዩ ዞኖች በተደረገው ግድያና መፈናቅል፣ በባሌ ጎባ፣ በአሰላና ሻሸመኔ አካባቢ በተፈጠሩ ግጭቶች ሁሉ ኦነግና የኦነግ ደጋፊዎች ስም መነሳቱ አሁንም ድርጅቱ በጥርጣሬ እንዲታይ አድርጎታል። ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቅኑ ኦሮሞዎች ኢላማ መደረጋቸው ደግቦ ችግሩን የበለጠ የተዎሳሰበ ያደርገዋል። ለምሳሌ ዶክተር አብይ እንደተናገሩት ዛሬ ኦሮሞና ኦሮምያ ብንልም አጋጣሚው ቢገኝ እንኳ ነገ ደግሞ የሸዋ፣ የአርሲ፣ የባሌ፣ የዎለጋና የሃረር በመባባል እንደምንከፋፈል ግልጽ ነው ያሉት ዛሬም በመሬት ላይ ያለ እውነት ነው። ብዙ ከሸዋ የተዎለዱ ወገኖቻችን በሁለት አቅጣጫ የተዎጠሩ እንድሆኑ ይናገራሉ። በአንድ በኩል ኦሮሞ የሚል በሌላው ማህበረሰብ ዘንድ የሚታዎቅ ማንነት ቢኖራቸውም በአክራሪ የኦሮሞ ብሄርተኞች ዘንድ ግን እናንተ ንጹህ ኦሮሞዎች አይደላችሁም ስነልቦናችሁ ለአማራ የቀረበ ነው በማለት እንደሚገለሉ ይናገራሉ። ለዚህም የበርካታ የኦሮሞ ልጆች የፌስቡክ መልእክት መመልካት አዲስ አይደለም።እስካሁን እንደተመለከትነው ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ማንነት የሌለው ተደርጎ

ስለተነገረ በድርጅቶች ላይ ጥርጣሬ ሲነገብ ተኑሯል። ለዚህ ነው የአቶ ለማና የዶክተር አብይ አባባሎች የተለየ አስደሳች ሆነው የዎጡት።

በመሰረቱ የኦሮሞ ህዝብ የኢትዮጵያ መስራችና ምሰሶ ከሆኑት ሌሎች ነገዶች አንዱ ነው። በታሪካችን አቡነ ጳጥሮስ የሌሉባት ኢትዮጵያ፣ የአበበ ቢቄላን ማንነት የካደች አገር፣ የአብዲሳ አጋን ጀግንነት የማታውቅ ኢትዮጵያ የለችንም። በኢትዮጵያ መንግስታት ታሪክ መሪዎች ዎይም ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ወይም ሚኒስትሮች ኦሮሞዎች ነበሩ። ለረዥም ዓመታት ኢትዮጵያን በንጉስነት የመሯት አጼ ሃይለ ስላሴ ግማሽ ኦሮሞ ነበሩ፣ መንግስቱ ሃይለማሪያም ኦሮሞ መሆኑን በአደባባይ ተናግሯል።ኦሮሞነት ከኢትዮጵያዊነት ተለይቶ የሚታዎቅ አይደለም። ብዙ ጊዜ የኦርሞ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያዊነትን ለዐማራ ብቻ ለምን እንደሚሰጡ አይታዎቅም። ዐማራ በራሱ እንዲደራጅ ምሁራንም ይሁኑ ፖለቲከኞች ሲያሳስቡ ከመጥፋትና ከፍትሃዊነት አንጻር እንጂ ኢትዮጵያን ከማፍረስ አንጻር አይደለም። ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ያለው የኢትዮጵያ ህዝብም የዐማራን ኢትዮጵያዊነት ለአፍታ ያክል እንኳ ተጠራጥሮ አያውቅም። የኦሮሞ ድርጅቶች ላይ የተሰራው ጸረ ኢትዮጵያዊነት ፕሮፓጋንዳ ግን ባንቀበለው እንኳ ተጽእኖው የበረታ ነበር።ከዚህ በተጨማሪ የዚህ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ የሆኑ የኦሮሞ ድርጅቶችን በተግባር ማየት ግን አሳሳቢ ብቻ ሳይሆን እውነትን በድፍረት እንዳንናገር ወንድሞቻችንን ከኩርፊያ ለማዳን ስንሞክር ኖረናል። ያ ፈጽሞ ስህተት ነበር። ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን ጃዋር መሃመድን ሆ ብለን አጭብጭበን ተቀበልነው።ጃዋር እስካሁንም ቢሆን ለተናገራቸውና ለቀሰቀሰበት ጸረ ኢትዮጵያዊና ጸረ አማራ ፕሮፓጋንዳ በይፋ ይቅርታ አልጠየቀም። ይህ ብቻ አይደለም ዛሬም አጋጣሚዎች በተፈጠሩለት ጊዘ የሚያስተላልፋቸው መልእክቶች አደገኞች ናቸው። ከላይ ማንሳት እንደሞከርኩት በርካታ ኦሮሞዎችን ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር መነጣጠል አንችልም። ዛሬም ቢሆን ከፖለቲካ መሪዎች ጀምሮ እስከ ታዋቂ አርቲስቶች፣ የሃይማኖት አባቶች ፣ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች ነገድ መናገር አስፈላጊ ከሆነ ኦሮሞ የኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት ነው። ኢትዮጵያዊነት ኦሮሞነት ነው፤ ኦሮሞነትም ኢትዮጵያዊነት ነው። እንደ አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ በቤተ መንግስት ኦሮሞ ባለመኖሩ አልካፈልም ብየ ሄጃለሁ የሚባልበት ኦሮሞነት በአካባቢ ሰውነት የሚለካበት ሳይሆን ቢገባውና ቢረዳው ኖሮ ከተጋበዙት አርቲስቶች ወደ ግማሽ የሚሆኑት በደማቸው ኦሮሞዎች መሆናቸውን ባዎቀና በንግ ግሩ ባፈረ ነበር። በብሄራዊ ትያትር፣ በአገር ፍቅር ትያትር፣በባህል አዳራሽ፣ በበርካታ የግል ሲኒማ ቤቶችና በበርካት የአማርኛ መጽሃፍት ድርሰቶች ስመጥር ባለሙያዎች ኢትዮጵያዊነት ያንገበገባቸው ኦሮሞዎች Commented [AT1]: መሆናቸው አልታየውም።

አሁን ባገኘው ዝናና ጭብጨባ መንደርተኝነት እንጅ አገር ስላልታየው ኦሮሞነትን ኦሮምኛ ቋንቋ ከመናገር ጋር ብቻ አያያዘው፤ በዚያ ላይ የጎሳ ማንነት እንጂ ዜግነትን ባንቋሸሸ ፕሮፓጋንዳ ስላደገ ሊፈረድበት አይችልም። ማጠቃለያ አላማየ በርካታ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያጎሉ የኦሮሞ ልጆችን ማስተዋወቅ አይደለም። ተወደደም ተጠላ አሁን የዘርና የጎሳ ፖለቲካ እንዲቀጥል ኢፍትሃዊ የሆነው ህገመንግስት በስራ ላይ እንዲቆይና የጎሳ ግጭቶችም የበለጠ ስር እንዲሰድዱ እየተደረገ ያለው የዘር ፈደራሊዝሙ እንዳይፈርስ ኦሮሞን በመሳሪያነት በመጠቀም ወንጀለኛ ድርጅቶችንም በማበረታታት ነው። ሃገራችን የሁላችንም እንጂ ለተዎሰነ ቡድን አይደለችም። ትግላችን ሊሆን የሚገባውም እኩልነትን፣ ፍትህንና ዲሞክራሲን ማስፈን ላይ ነው። ጎሳን የዎንጀለኝነትና ኢትዮጵያን ማፍረሻ መሳሪያ ማድረግ ወይም ወንጀል ሰርተን መደበቂያ ማድረግ አይገባንም። ስለዚህ ዶክተር አብይ የመጀመሪያ ስራቸውና እርምጃቸው ዜጎችን እኩል መመልከት ካቃተው ህገ መንግስት በመነሳት ኢፍትህአዊነት የሰፈነባቸውንና ኢዲሞክራሲያዊ ህጎችን ማፍረስ ላይ መሆን ይኖርበታል። ያኔ የእውነተኛ ለውጥ ባለቤት መሆን እንችላለን። ሃገራችንን እግዚአብሔር ይባርካት። ጨረስኩ!!!

©አዲስ ተስፋ

ጥቅምት 2018